# የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን

# ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ኢንዱስትሪዎች ጋር የፈቃደኝነት የኢነርጂ ብቃት/ቁጠባ/ ስምምነት ማስፈፀሚያ መመሪያ

2019

## አንቀፅ 1
## አውጪው ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን በኢነርጂ አዋጅ 810/2006 አንቀፅ22/1/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አንቀፅ 2
## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ኢንዱስትሪዎች ጋር የሚደረግ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የፈቃደኝነት ስምምነት ማስፈፀሚያ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 3
## ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በኢነርጂ አዋጅ 810/2006 አንቀጽ 22/1/ መሰረት የተለያዩ ፈጣንና ወሳኝ የኢነርጂ አጠቃቀም ማሻሻያ ዘዴዎችን በመጠቀም የኢንዱስትሪዎችን የኢነርጂ ፍጆታ አሁን ካለበት ደረጃ መቀነስ መቻል ነው፡፡

## አንቀፅ 1
## ትርጓሜ

በኢነርጂ አዋጅ 810/2006 እና በኢነርጂ ደንብ ቁጥር 447/2011 የተቀመጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ያገለግላል፡፡

## አንቀፅ 5
## ሕጋዊ ማዕቀፍ

በብሔራዊ ደረጃ የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የፈቃደኝነት ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን መስራት እንደሚችል በኢነርጂ አዋጁ ተደንግጓል፡፡ በኢነርጂ አዋጅ 810/2006 አንቀጽ22/1/ የፈቃደኝነት ስምምነቶች ግልፅና የማያሻማ ዓላማዎችን እንዲሁም ዓላማዎቹም የማይፈጸሙ ወይም ሊፈፀሙ የማይችሉ የሚሆንበት ጊዜ ወደ ተሻሻሉ ወይም ወደ ተጨማሪ እርምጃዎች ሊመሩ የሚያስችሉ ክክትትልና ከሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶች ጋር የተያያዙ ስርዓቶች ሊኖሯቸው ይገባል፡፡

## አንቀፅ 6
## ውል ፈፃሚ አካላት

ይህ የኢነርጂ ብቃት/ቁጠባ ስምምነት የሚፈፀመው በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ 308/2006 የተቋቋመ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣንና ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ በሆኑ ኢንዱስትሪ መሀከል ነው፡፡

## አንቀፅ 7
## መሰረተ ሀሳብ

የኢንዱስትሪው ሴክተር በኢትዮጵያ በከፍተኛ ሁኔታ በማደግ ላይ የሚገኝ ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ዘርፍ ነው፡፡ በአብዛኛው የማምረቻ ፋብሪካዎች ላይ ከፍተኛውን ወጪ ከሚያስወጡት ውስጥ አንዱ ለኢነርጂ

የሚወጣው ወጪ ነው። ይህንን የኢነርጂ ፍጆታ በመቀነስ ኢነርጂ ብቃትን አሻሽሎ ፋብሪካዎች ወጪያቸውን በመቀነስ ቀጣይነት ያለው ተወዳዳሪነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ስለዚህ ውጤታማ የሆነ የኢነርጂ ማኔጅመንት ሲስተም በመተግበር ለተሻለ ትርፋማነትና ቀጣይነት ወሳኝ ነው።

በ2011 ዓ.ም የፀደቀው የኢነርጂ ደንብ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን በተመረጡ ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ኢንዱስትሪዎች ላይ ኢነርጂ ብቃት እንዲያስፈፅም ኃላፊነት ተሰጥቶታል። የሀገሪቱን ኢነርጂ ፖሊሲ ለመተግበርና ኢንዱስትሪዎች ላይ ኢነርጂ ብቃት ለማሻሻል ባለስልጣኑ ከ ኢንዱስትሪዎች ጋር የሚፈፅመውን የፈቃደኝነት ስምምነት ወሳኝና ወጪ ቆጣቢ መሳሪያ አድርጎ ይመለከተዋል።

የኢነርጂ ብቃት ስምምነት ፕሮግራም በመተግበር ባለስልጣኑ የሀገሪቱን የኢነርጂ ፖሊሲ ለመተግበር ወሳኝ ሚና የሚጫወተውን የኢነርጂ ቁጠባ እና ኢነርጂ ብቃት ማሻሻያ ዘዴ ይጠቀማል።

## አንቀፅ 8
## ማብራሪያ

### 8.1. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ

በዚህ ስምምነት ኢነርጂ ቁጠባ ማለት ለታለመለት የመጨረሻው የኢነርጂ ፍጆታ አሁን ካለበት ደረጃ ፈጣንና ወሳኝ ዘዴዎችን በመጠቀም መቀነስ መቻል ነው። እንዲሁም የተለያዩ የማሻሻያ ተግባራዊ እርምጃዎችን በመውሰድና ባለመውሰድ ያለውን የኢነርጂ ፍጆታ በንፅፅር ማሳየት መቻል ነው። በዓመት የተቆጠበ ኢነርጂ መጠን የሚወሰነው በልኬትና በስሌት ሲሆን ፍጆታው የሚገመተው የኢነርጂ ብቃት ማሻሻያ ከተተገበረ በኃላና በፊት ያለውን ልዩነት ና አካባቢያዊ/ውጫዊ/ ሁኔታዎችን ኢነርጂ ፍጆታ ላይ ተፅዕኖ እንዳያሳድሩ በመቆጣጠር ይሆናል።

በተጨማሪም የኢነርጂ አጠቃቀም ብቃት ማሻሻል ማለት አንድን ምርት/አገልግሎት/ ለማምረት የሚያስፈልገውን የኢነርጂ መጠንን የኢነርጂ ቁጠባ ዘዴዎችን በመጠቀም መቀነስ መቻል ነው። የኢነርጂ ብቃት ማሻሻያ ዘዴዎች ቴክኒካል ከሆኑ ወይም ኃይል ተጠቃሚ መሳሪያዎች/ዕቃዎች/፣ የብቃት ማሻሻያ ቅደም ተከተሎችን፣ ከስራ አካባቢን ወይም ባህሪ ጋር የተቆራኘ ነው።

### 8.2. ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ኢንዱስትሪ

በዚህ የውል ስምምነት ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ኢንዱስትሪ ተብሎ ለዚህ ዓላማ የተጠቀሱት ዓመታዊ ኢነርጂ ፍጆታቸው ከፍተኛ የሆኑ ኢንዱስትሪዎችን ሲሆን ይህም በዓመት 22 GWH ኢነርጂና ከዚህ በላይ የሚጠቀሙትን የሚያጠቃልል ነው።

### 8.3. ኢነርጂ ማኔጅመንት ሲስተም

ኢነርጂ ማኔጅመንት ሲስተም ማለት የኢነርጂ ብቃትን በፋብሪካዎች ውስጥ በቀጣይነት ለማሻሻል ከፋብሪካው መመሪያና የምርት ሂደቶች አንፃር የሚያስፈልጉትን አነስተኛ መስፈርቶች የሚዘረዝር

/የሚገልፅ/ ዘዴ ነው። ሲስተሙ ከሚያካታቸው ውስጥ ለምሳሌ የኢነርጂ ብቃት ስራዎችን ማደራጀት፣ የኢነርጂ ብቃት ግብ፣ ኢነርጂ ብቃት ማሻሻያ እቅድ፣ ኢነርጂ ብቃትን ከግምት ውስጥ ያስገባ የኤሌክትሪክ መሳሪያዎችንና ዕቃዎችን መጠቀም እና የኢነርጂ ፍጆታን መከታተልና በየዓመቱ ሪፖርት ማድረግን ይመለከታል። የኢነርጂ ማኔጅመንት ሲስተም መዋቅር የISO 50001 ኢነርጂ ማኔጅመንት ደረጃን የሚከተል ሲሆን ነገርግን መስፈርቶቹ ጠቅለል ባለ መልኩ ይገለጻል።

### 8.4. ውል ፈፃሚ አካላት

በዚህ ስምምነት ፈፃሚ አካላት የሚባሉት የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን እና ለስምምነት የተመረጠው ኢንዱስትሪ ነው።

## አንቀፅ 9
## ዓላማዎችና የስምምነት ጊዜ

### 9.1. የስምምነቱ ዓላማዎች

የዚህ ስምምነት ዓላማ ኢንዱስትሪዎች የኢነርጂ አጠቃቀም ብቃታቸውን በማሻሻል የኢነርጂ ፍጆታቸውን እንዲቀንሱ ማስቻል ነው። የኢንዱስትሪዎች የኢነርጂ ቁጠባ ግብ የሚገለፀው ኢንዱስትሪዎች ባስቀመጡት መርሃ ግብርና በተወሰነ የጊዜ ገደብ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን ዓላማ የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የፈቃደኝነት ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን በመስራት አጠቃላይ ካሉት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 80 በመቶ የሚሆኑትን በዚህ የፈቃደኝነት ስምምነት ስር እስከ እ.አ.አ 2021 መጨረሻ ድረስ ማካተት ነው።

### 9.2. ስምምነት የሚከናወንበትና የሚቆይበት ጊዜ

የስምምነት ጊዜው ስምምነቱ ከተፈፀመ ጊዜ አንስቶ እስከ 3 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን እስከ እ.አ.አ ከ2021 በኃላም ሊራዘም ይችላል።

## አንቀፅ 10
## የኢንዱስትሪው ግዴታዎች

ኢንዱስትሪው ያዘጋጀውን መርሃ ግብር ቀጣይነት ባለው መልኩ የኢነርጂ ብቃት ለማሻሻል ኢነርጂ ማኔጅመንት ሲስትምን ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል። ከዚህ በታች ያሉት ከኢንዱስትሪው የሚጠበቁ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው።

1. የኢነርጂ ፖሊሲ በፅሁፍ ያዘጋጃል፣
2. ኢነርጂ ማኔጅመንት ዩኒት ያቋቁማል፣
3. በፋብሪካው ዉስጥ የኢነርጂ ማኔጅመንት ዓላማዎችን ያስፋፋል፣

4. ኢነርጂ የመቆጠቢያ ዘዴዎችን በተመለከተ፣ ተገቢ የሆነ ፋይናንስ እና ኢንቨስትመንት ይመድባል፣
5. የኢነርጂ ፍጆታ ግብ እና መነሻ በማስቀመጥ፣ ግቡን ለማሳካት ይሠራል፣
6. ቢያንስ በየ 3 ዓመት ኢነርጂ ኦዲት መሠራቱ ያረጋግጣል፣
7. ሥምምነቱ ከተፈፀመ በኃላ፣ የተለያዩ የኢነርጂ ቁጠባ ዘዴዎች፣ አተገባበር፣ ጠቅላላ የኢነርጂ ፍጆታ፣ የኢነርጂ ብቃት ማሳያዎች እንዲሁም የተገመተው የኢነርጂ እና የገንዘብ ቁጠባ ለባለሥልጣኑ ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣
8. የፍቃደኝነት ሥምምነት ከመፈፀሙ በፊት የኢነርጂ ኦዲት ሥራ ያከናወናል፡፡

### 10.1. የኢነርጂ ማኔጅመንት ዩኒት ኃላፊነት

1. የሶስት ዓመት መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣
2. የISO 50001 ፎርማትን በተከተለ መልኩ የኢነርጂ ማኔጅመንት ሲስተም ያቋቁማል፣
3. የኢነርጂ ቁጠባ ዘዴዎችን በመለየት ይተገብራል፣
4. ኢነርጂ ፍጆታን ይቆጣጠራል፣
5. ኢነርጂ ኦዲት ያከናወናል ወይም በባለስልጣኑ የኢነርጂ ኦዲት ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ እንዲከናወን ያደርጋል፣
6. የኢንዱስትሪው ሠራተኞች ኢነርጂ ኢንዲቆጠቡ የግንዛቤ ስራ ይሰራል፣
7. የተገኘዉ ዉጤት በመገምገም እና በመቆጣጠር ለኢንዱስትሪው የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## <u>አንቀፅ 11</u>
## <u>የባለስልጣኑ ኃላፊነት</u>

1. ከኢንዱስትሪ ተወካዮች እና ከሌሎች የሥምምነት ትግበራ ፕሮግራም ተሳታፎዎች ጋር በመሆን የኢነርጂ ብቃት ሥምምነት እቅድ ያዘጋጃል፣
2. ለኢንዱስትሪዎች የኢነርጂ ብቃት ሥምምነት የአፈፃፀም ግብ ይቆጣጠራል፣
3. ኢነርጂ ብቃትን ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ ኢንዱስትሪዎች ጋር ለማነፃፀር የኢነርጂ መነሻ ነጥብና ማመሳከሪያ/baseline/ ያዘጋጃል፣
4. ከሌሎች የሥምምነት አካላት ጋር በመሆን የስምምነቱ ክንዋኔ ጋር ተዛማጅነት ያለው የልማት እና የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ ላይ ይሣተፋል፣
5. የኢንዱስትሪዎችን የሥምምነት ግደታዎች አፈፃፀም ይቆጣጠራል፣ የሥምምነት ግዴታ ሳይፈፅም ሲቀር ለኢንዱስትሪው ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ለቀጣይ ሥራ ለኢንዱስትሪው የማኔጅመንት ቡድን የመፍትሄ ሀሳብ እቅድ (proposal) አዘጋጅቶ ያቀርባል፣
6. በማንኛዉም ምክንያት የተስተጓጎለዉን ዓላማ ለማሳካት ዳግም ተጨማሪ ዘዴዎችን ይከልሳል፣
7. በቅናሽ ዋጋ ወይም በነፃ ለኢነርጂ ብቃት ባለሙያዎች ተገቢ የሆነ ሥልጠና ይሠጣል፣

8. በኢነርጂ ብቃት የቴክኒካል እና የምክር አገልግሎቶችን ድርጅታዊ እና የፈንድ አተገባበር ላይ ይሳተፋል፣
9. ፈቃድ ባለዉ የኢነርጂ ኦዲት ባለሙያ በሚሠራ የኢነርጂ ኦዲት ሥራዎችን ይቆጣጠራል፣
10. በኢንዱስትሪ የቀረበዉን ሪፖርት በመገምገም የማሻሻያ ሀሳብ (recommendation) ይሰጣል፣
11. የኢነርጂ ብቃት ሥራዎችን የሚተገብሩ ኢንዱስትሪዎች የኢነርጂ ብቃት ፈንድ እንዲያገኙ ያመቻቻል፣
12. በተቻለ መጠን ለዘላቂ እና ምቹ የሥምምነት ትግበራ የቴክኒክ ምክር እና ድጋፍ ይሰጣል።

## አንቀፅ 12
## ስምምነቱ የሚፈጀው ጊዜ

ይህ የኢነርጂ ብቃት ሥምምነት ሥራ ላይ የሚዉለዉ የፊርማ ስነ-ሥርዓት ከተፈፀመ በኃላ ነዉ። ሥምምነቱ ፊርማው ከተፈረመ ጀምሮ ለ 3 ዓመት ህጋዊ ሆኖ ይቆያል። እንደ ኢንዱስትሪዎች ሁኔታ እና ግዝፈት (በፋይናንስ እና ትልቅነት) የተቀመጠዉን ኢነርጂ ግብ ለመቆጠብ የሚያስፈልገዉን የማስፈፀሚያ ጊዜን ባለሥልጣኑ ያስቀምጣል።

## አንቀፅ 13
## ስምምነትን ስለማቋረጥ ወይም ስለማደስ

የስራ ሁኔታ ወይም አካባቢው በመሰረታዊነት ከተቀየረ፣ በስምምነት ፊርማ ጊዜ ካለው ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ወይም ስምምነቱ ለተቀመጠለት አላማ ውጤት ካላመጣ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን ስምምነቱን ሊያቋርጥ ወይም ሊያድስ ይችላል። ስምምነቱ በጋራ መግባባት ከተቋረጠ ከኢንዱስትሪዎች ኢነርጂ ብቃት ስምምነት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁሉም መርሃ ግብሮች የሚቋረጡ ይሆናሉ። የአመራር ቡድኑ በስምምነቱ መሰረት ያልተፈፀሙ ወይም ፍፃሜ ያላገኙ ፕሮጀክቶችን እንዴት መፈፀም እንዳለባቸው ስምምነት ያደርጋል።

## አንቀፅ 14
## ኢንዱስትሪው ከስምምነት ስለመውጣት እና የሚያስከትለው ውጤት

ኢንዱስትሪው ለኢነርጂ ባለስልጣን እና ተዛማጅ ለሆኑ ኢንዱስትሪ ማህበራት ፅህፍ በማቅረብ ከኢነርጂ ብቃት ስምምነት መውጣት ይችላል። ኢንዱስትሪው ከስምምነት መውጣቱን ባሳወቀበት ጊዜ በኢነርጂ ብቃት ስምምነት ሲደረግ የወሰደውን ማንኛውንም ኢነርጂ ድጎማ ሪፖርት ማድረግ አለበት። በዚህ ስምምነት መሰረት የተፈፀመውን የኢነርጂ ድጎማ እና ኢንዱስትሪው ስምምነት ሲያቋርጥ የወሰደውን ድጎማ እንዲመልስ በተወሰነው መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል። በኢነርጂ ባለስልጣን የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት ወይም ድጋፍ በባለስልጣኑ ሰራተኞች ወይም አማካሪዎች በገበያ ዋጋ መሰረት ሊሰጥ ይችላል (ሂሳቡ በኢነርጂ ባለስልጣን የሚሰላ ይሆናል) እና ለዚህ ስምምነት አላማ ተብሎ የተደረገ ድጎማ መሆኑን

ግምት ውስጥ የሚገባ ሲሆን ለነዚህ ወጪዎች ኢንዱስትሪው ለኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን የሚያወራርድ ይሆናል። ባለስልጣኑ የፈፀመውን ድጎማ በመሰብሰብ ላይ ለእያንዳንዱ ጉዳይ በተናጠል ይወስናል።

### 14.1. ኢንዱስትሪውን ከኢነርጂ ብቃት ስምምነት ስለመሰረዝ እና የሚያስከትለው ውጤት

ኢንዱስትሪው በስምምነት ወቅት የገባውን ግዴታዎች የማያሟላ ከሆነ ከስምምነት የሚሰረዝ ይሆናል። የኢንዱስትሪው በገባው የስምምነት ግዴታ መሰረት ወይም ለኢነርጂ ብቃት የስምምነት ፕሮግራም የቁጥጥር ስርአት የተጠየቀውን መረጃ ሪፖርት ማድረግ እያለበት ይህን በተደጋጋሚ ካልተገበረ ከስምምነቱ ይሰረዛል።

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን የስምምነቱን ግዴታ አለመተግበሩን ለማጣራት ለኢንዱስትሪው የሚያሳውቅ ይሆናል። ኢንዱስትሪው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ስራውን በትክክል ካላስተካከለ የኢነርጂ ባለስልጣን ተጨማሪ የማሻሻያ ሃሳብ አዘጋጅቶ የሚያቀርብ ይሆናል። በዚህ ስምምነት መሰረት የተፈፀመውን የኢነርጂ ድጎማ እና ኢንዱስትሪው ከስምምነቱ ሲሰረዝ የወሰደውን ድጎማ እንዲመልስ በተወሰነው መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል። ይህን ድጎማ የሰጠው ባለስልጣን በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በተናጠል ውሳኔ ይሰጣል።

## <u>አንቀፅ 15</u>
## <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ በሚሸፍናቸው ስራዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## <u>አንቀፅ 16</u>
## <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

አውጪው ባለስልጣን ይህንን መመሪያ ከሶስት ዓመትበኃላ ሊያሻሽለው ይችላል።

## <u>አንቀፅ 17</u>
## <u>የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

---------------------------------

ዶ/ር ፍሬሕይወት ወ/ሐና

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን የቦርድ ሰብሳቢ

አዲስ አበባ፣ ---------/----------/2011 ዓ.ም

## ቅጥያ (Annex) 1

### በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 22 እና በኢነርጂ ደንብ ቁጥር 447/2011 አንቀጽ 52 መሠረት የተደረገ የኢነርጂ ብቃት የፈቃደኝነት ስምምነት

የፈቃደኝነት ስምምነት ሰጪ : የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን

የፈቃደኝነት ስምምነት ተቀባይ : ______________________________

ይህ ከከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ኢንደስትሪዎች ጋር የፈቃደኝነት የኢነርጂ ብቃት ስምምነት ማስፈጸሚያ መመሪያ ጋር ቅጥያ (Annex) የተደረገው የኢነርጂ ብቃት የፈቃደኝነት ስምምነት ፎርም ሲሆን የስምምነቱም አፈጻጸም በመመሪያው ቁጥር ________ መሠረት ይሆናል፡፡

የኢነርጂ ብቃትን ለማሻሻል ኢንዱስትሪው በሚያወጣው የኢነርጂ ብቃት ማሻሻያ አተገባበር እቅድ (Action Plan) መሠረት የተለያዩ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ሥስራዎችን (Energy Efficiency and Conservation Measures) እና በመመሪያው ላይ የተጠቀሱትን ኢንደስትሪው በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዙሪያ ላይ የተሰጡትን ሀላፊነቶችን (Responsibility of the Industry) በመተግበር ኢንደዲትሪው ይጠቀም የነበረውን ዓመታዊ የኢነርጂ ፍጆታ መጠን በዓመት ____________% ለመቀነስ ፋብሪካው ከስምምነት ሰጪው ጋር ተስማምቷል፡፡
ስምምነቱ የሚቆይበት ጊዜ፡ ስምምነቱ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ለሶስት ዓመት ይቆያል፡፡

**የፈቃደኝነት ስምምነት ሰጪ፡**

ስም ______________________________

ፊርማ ______________________________

**የፈቃደኝነት ስምምነት ተቀባይ**

ስም ______________________________

ፊርማ ______________________________

ቀን : ______________________________

**ማሳሰቢያ**

- *የዚህ ስምምነት አንድ ቅጂ ለስምምነት ሰጪው አካል ቀሪ ሲሆን አንድ ኮፒ ደግሞ ለስምምነት ተቀባይ ይሰጣል፡፡*